# አጽማቸውን የፈለሰው መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ድህረ አምስቱ ዘመን ተጋድሎ

# ክፍል ሁለት


## ቀሲስ አስተርአየ

(nigatuasteraye@gmail.com) ነሐሴ ሁለት ሺህ ዘጠኝ ዓ.ም


*የምናውቀውን እንናገራለን ያየነውን እንመሰክራለን (ዮሐ 3፡11)*

ጣልያን የደመሰሰውን መልሶ ለመግንባት፤ ያፈረሰውን ለመስራት፤ ያናጋውን ለመጠገንና የኦርቶዶክስን እምነት ጠልቀው ባልተረዱ ሰሞነኞች ካህናት ጭንቅላት ላይም የከተተባቸውን የተዛባ የነገረ መለኮት አተላ ለማጽዳት መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ኃይላቸውን አሰባስበው በብቸና አውራጃ መንቀሳቀስ ጀመሩ። በዚህ ላይ



እያሉ ባምስቱ የጦርነቱ ዘመን ከጣሊያን ጋራ በገጠማቸው ሞትና ሽረት ትንቅንቅ ላይ ከገጠማቸው የባሰ እጅግ የከፋና መፈጠራቸውን እንዲጠሉ ያደረጋቸው መራራ ነገር ተከሰተ። ኃይሉን በካባቢው ከነበሩት አርበኞች ጋራ አቀናጅቶ፣ምክራቸውንና መመሪያቸውን እየተቀበለ በፍጹም ወኔና ጀብዱ ፋኖዎችን እየመራ፤ ባንዳዎችን እየገረፈ የሞሶሎኒን ጭንቅላት እንደ እባብ የቀጠቀጠውን በላይ ዘለቀን በጦር ሜዳ ያልዋሉ ባንዳዎች ነጻ ባወጣት በኢትዮጵያ ምድር በየተኛውም አገር ባልተፈፀመ የግፍ ፍርድ እንደ እስስት ታንቆ እንዲገደል ፈርዱበት።

ኢትዮጵያ ደም መላሽ ብላ የሰየመችውን ጀግና፤ ኢትዮጵያውያን ባንዶች በጠላትነት ፈርጀው በመግደላቸው፤ ለየጣሊያኖች ደም ተበቅለው በላይን ወደ ሚሰቀሉበት መስቀል ሲወስዱት **"አንቺ አገር ወንድ አይብቀልብሽ!"** አለ እንደሚባለው፤ ዛሬ እናት ኢትዮጵያ እንደ

በላይ ያለ ልጅ በማጣቷ ባህሯን አጣች፣ ሱዳን ቦጭቆ በላት፣ ቻይናው፣ አረቡ፣ ህንዱና ፓኪስታኑ መሬቷን ተቀራምቶ ወረራት።

በላይ ዘለቀ ከሞተ ከሰላሳ ዓመታት በላይ ያልኖሩ የተረገሙ ኢትዮጵያውያን፤ በላይን እንደ ክርስቶስ በአደባባይ በመስቀል ጣልያን ሊያደርገው ያልቻለውን የጣልያን ምኞት ፈጸሙለት።

መላከ ብርሃን አድማሱ የመንፈስ ልዕልና ምሳሌ አድርገው በሚቆጥሩት በበላይ ዘለቀ ላይ የተፈፀመው ይህ ግፍ በታገለላትና ነጻ ባወጣት በኢትዮጵያ ምድር መፈፀሙ፤ ህሊናቸውን አናወጠው።

በኋላው፣ በፊቱና በጎኑ የተጠመደበት ወጥመድ ያልያዘውን የተተኮሰበት የጥይት እሩምታ ያልገደለውን ባንዳዎች እንደ እስስት በገመድ አንቀው በላይን በገደሉበት ወቅት፤ አገሩን ነጻ አውጥቶ ከጣሊያን የመርዝ ጢስ የጸዳ አየር ተንፍሶ፣ እየጠጣ ያሳደግችውን በጎይ ጊርጊስ አካባቢ የምትመነጨውን ንጹህ ውሀ ጠጥቶና የመንፈስ እረፍት አግኝቶ ገና አልተረጋጋም ነበር።

በላይን ተከትለው ሲፋለሙ የወደቁት ፋኖዎች፣ ጣልያን የጨፈጨፋቸው እናቶች፤ልጆችና አዛውንት አብረው ከበላይ ጋር ሲሰቀሉ፣ ጀግንነትና ወኔም አብረውት በገመድ ሲታነቁ ታዩአቸው። ይህ ሁሉ ተደራርቦ ሐዘኑ በላያቸው የነደደ እሳት ሆኖ መላከ ብርሃን ተቃጠሉ። አረሩ። ከሰሉ።

በሀዘን ከሚሰበቀው አንጀታቸው ግፊት የሚፈሰው እንባ ፊታቸውን እንደ ጎርፍ አጥለቀለቀው። ይህ የሀዘን ስሜት ባምስቱ የመከራ ዘመን አብረው የተጌዙትን የመላከ ብርሀንን ስሜት ይቅርና፤ ይህን ታሪክ የሚያነበውን ጤናማ አእሞሮ ያለውን ሁሉ ኢትዮጵያዊ ስሜትና ቅስም ሲሰብር የሚኖር ነው።

እንደ መላከ ብርሃን አድማሱ የጎጃም ሕዝብ በሐሰት በከሰሱት፣ እንዲገደል በፈረዱት፣ ፍርዱን ባስፈፀሙትና እንዲሰቀል በተባበሩት እጅግ አዝኖ ማንጎራጎርና መቀኘት ጀመረ። ።

እንዲሰቀል የከሰሱትን፣ የመሰከሩበትንና የፈረዱበትን የባንዳዎችን ደካማናትና ሱሪ አልባነት ለመግለፅ፦

የበላይን ሱሪ ሰፊ አበላሽቶበት

ምናምንቴ ሁሉ ጉልበቱን አየበት¡ ብሎ ህዝቡ ገጠመ።

በላይን የሚያህል የልዕለ አዕምሮ ምንጭና፣ ያገር መከታ እንደ እስስት በገመድ አንቆ መገደል ይቅርና በኢትዮጵያ ምድር እሾህ ይወገዋል ብለው ጭራሽ ያልገመቱ ሰዎች በስቅላት መገደሉን መቀበልና ማመን አቃታቸውና፦

ተሰቀለ ቢሉኝ መውዜሩ ነብየ

ተሰቀለ ቢሉኝ አልቢኑ ነው ብየ

ለካ በላይ ኖሯል ትልቁ ሰውየ¡ ብለው ለበላይ ተቀኙለት። ሰቅለው በገደሉትም ባንዶች ተቀኙባቸው።

ከሆዳቸው በቀር ግራ ቀኝ የማያዩ፤ በሰውነታቸው ውስጥ ያለው የተፈጥሮ ሞት ጊዜውን ጠብቆ የሚፈነዳባቸው መሆኑን የላሰቡትን እንስሶች፦ በበላይ ላይ በፈጸሙት የግፍ ፍርድ፦

አገሬ ኢትዮጵያ ሞኝ ነሽ ተላላ

የሞተልሽ ሞቶ የገደለሽ በላ እያለ የኢትዮጵ ህዝብ አጋለጣቸው።

የበላይን ህይወት ለማጥፋት ብዙ ገንዘብ አፍሶ፤ ያለ የሌለውን ሁሉ መላ ተጠቅሞ ጣሊያን ያልተሳካለትን፤ አገር በቀል ጠላቶች በላይን አታለው ወስደው ገድለው ከጣሊያን ጋራ መታረቂያ አደረጉት" ብሎ ህዝቡ ተቆጣ። በዚህ ግፍ የተበሰጨው ህዝብ ገዳዮችን ተጸይፎና ንቆ ለሽፍትነት ሲዘጋጅ፤ "ጣሊያንን ሲዋጉ በወደቁት ወገኖቻችን ላይ የደረሰብን ሐዘን ሳንጨርስ ለሌላ እልቂት አንዘጋጅ" የሚሉ ሽማግሎች የተቀሰቀሰውን ህዝባዊ ቁጪት አበረዱት።

የጣልያንን ቅስም የሰበረው የበላይ ዘለቀ በስቅላት መገደል የጎዳቸው መላከ ብርሀን አድማሱ ጀንበሬም፤ ኢትዮጵያ ከጣሊያን አካላዊ ወረራ

ብትላቀቅም፤ ጣሊያን ከተፋባት ከመንፈስ አተላና ከጣለባት ሞራል አላሻቂ እበት ገና እንዳልተላቀቀችና እንዳልጸዳች ተረዱ። የኢትዮጵያ መከራ ብዙ እንደሆነ በመመልከትና በግላቸው ምን ማድረግ እንዳለባቸው ለማሰብ፤ ማንንም ሳያማክሩ ከብቸና ጊዮርጊስ ደብር በታች ካለችው ጭለሚት ማርያም ከምትባለው ገዳም ገቡ።

ኢትዮጵያውያን ፈጣሪ የማይቀበለው ህዝብ የሚጎዳ ተግባር ሲፈጽም ሲያዩ፦ በመጸየፍና በመናቅ ለመፋለም፦

ጥራኝ ጫካው ኧረ ጥራኝ ዱሩ

ላንተም ይሻልሀል ብቻ ከማደሩ ብለው ወደ ጫካ እንደሚመነኑ፦

እንደ መላከ ብርሃን የመሳሰሉ መንፈሳውያን አባቶችም አመጸኛ መንግስት በህዝብ ላይ ሲያምጽ፤ ህዝብ ሲበድል የበዳዩን አጸያፊ ተግባር በመናቅ የንቀታቸውንም መልእክት በቅርብና በሩቅ ላለው ህዝብ ለማስተላለፍ ወደ ገዳም ይመንናሉ።

በነገራችን ላይ፦ ማመጽ ማለት በደል መፈጸም ማለት ነው። መንግስት በህዝብ ላይ በደል ሲፈጽም፤ በህጉ ላይ አመጸ፤ ሰባዊ ክብር አዋረደ ማለት ነው። ስለዚህ በቋንቋው ግንዛቤ አመጸኛ ማለት፤ ወንጀለኛ በደለኛ ማለት ሲሆን፤ አመጸ መባል የሚገባው ምንግስት እንጅ ህዝብ አይደለም ማለት ነው።

መንግስት በራሱ ህግ አመጸኛ ሲሆን፤ ሰባዊ ክብርን ሲገስ፤ ህዝብ መንግስትን ይመንናል። ይነቅፋል፤ ይጸየፋል፤ ይቆጣል፤ ይገስጻል፤ ከአመራሩም ራሱን ያገላል።

በተለያዩ ወቅቶች ብጹዕ ወቅዱስ አባታች አቡነ ባስልዮስ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ከነበረው ስርአት ርቀው ጎልቶ የሚታይ አመጽ በህዝብ ላይ ሲፈጽሙ፤ የተፈጸመውን ስህተት ንቀው የመናቃቸውንም መልእክት በቅርብና በሩቅ ላለው ህዝብ ለማስተላለፍ ደብረ ሊባኖስ ደጋግመው ገብተዋል። ንጉሡም እናስተካክላለን ብለው አማላጅ በመላክ ቃል በመግባታቸው አቡነ ባስልዮስ ወደ መንበረ ፓትርያርካቸው ተመልሰዋል።

ብጹዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስም፦ ቤተ ክርስቲያንን ከስርአተ መሳፍንቱ ያለቀቃትን ቃለ ዓዋዲ የተባለውን አዲስ ስርአት ባዘጋጁ ጊዜ ቀዳማዊ ንጉሥ ኃይለ ስላሴ እንዲስማሙላቸው፤ ባይስማሙላቸው ግን መንነው ወደ ገዳም እንደሚሄዱ አስቀድመው ስለ ገለጹላቸው፤ ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ በዙሪያቸው ከከበቧቸው መሳፍንት ባለጢሰኞች ጋራ ልማከር ሳይሉ፤ የራሳቸውን ስርአት የሚቃወመውን ቃለ ዓዋዲ የተባለውን አዲስ ስርአት በነጋሪት ጋዜጣ እንዲታወጅ አድርገዋል።

አርቀው ማሰብ ያቃታቸው እንስሶች በላይ ዘለቀን አንቀው በገደሉበት መንገድ፤ ማሰብ የተሳናቸው ደርጎችም አቡነ ቴወፍሎስን አንቀው የገደሏቸው፤ አቡነ ቴዎፍሎስ ደርጎችን ስለመነኗቸው ስለተጸየፏቸው እንጅ፤ ከደርግ ጋራ ተስማምተው ደርግ ታራሚ የሚለውን እያሉ ለመኖር ቢወስኑ ኖሮ፤ ደርግን መጥቀም የሚችሉት ከአቡነ ተክለሃይማኖት ይልቅ፤ በዓለም ተሰሚነት የነበራቸው አቡነ ቴዎፍሎስ ነበሩ። አቡነ ቴወፍሎስ አድር ባይ መሆንን ቢወዱ ኖሮ፤ ለደርግ መሳሪያ ለመሆን የሚያግዳቸው አልነበረም። አቡነ ተክለ ሃይማኖትም ቢሆኑ ባላወቁት መንገድ ተጠልፈው ቢገቡና ባዝጋሚ መረዳታቸው ጥቂት አመታት ቢወስድባቸውም፤ የደርጎች ስህተት ሲገባቸው ደርጎችን ተጸይፈው አትቅረቡኝ ብለው እንደሞቱ ይነገራል።

መንግስት በህዝብ ላይ የሚፈጸመው በደል ሲደራረብ ሸክሙ የሚከብደው በኦርቶዶክሳውያን መንፈሳውያን አባቶች ላይ ነው። ፓትርያርክ ሽኖዳም ህዝባቸው ሲበደል ብቻ አይደለም፤ ያንድ ካህን ባለቤት በመደፈሯ መንነው ገዳም ገብተዋል።

በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና አመራር ላይ የሚሰየሙ መንፈሳውያን አባቶች፤ በህዝብ ላይ ሸክም ከሚያከብድ መንግስት ጋራ ከመተባበር ገለል ብለው ራሳቸውን የሚፈትሹበት ለህዝባቸውም መልእክት የሚያስተላልፉበት መንግስትን ሚያጋልጡበት መሳሪያቸው መመነን ነው።

ኦርቶዶክሳዊው መላከ ብርሃን አድማሱም የጣሊያን ወረራ እንዳለቀ ወደ ደብረ ጥሞና የሄዱት፤ በላይ ዘለቀ ሲገደልም ወደ ጮለሚት ገዳም የመነኑት በቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ስርአት ነበር።

በበላይ የተፈጸመውን አረማዊ ተግባር መንነው ከብቸና ጊዮርጊስ መሰወራቸው ሲሰማ፤ በላይን ለማስገደል የተባበሩት ባንዶች በበላይ ዘለቀ ላይ ያደረጉትን በሰቸው ላይም ለመድገም፤ አንዴ በምንግስት ላይ ሸፈቱ፤ ሌላ ጊዜ ሃይማኖታቸውን ካዱ እያሉ አስወሩባቸው።

የደብሩ ሊቃውንትና ሕዝቡ ግን፤ አሁንም እንደ በፊቱ መላከ ብርሃንን አፈላልገው ከመነኑበት ከጮለሚት ማርያም ገዳም አገኙተው ወደ ቦታቸው እንዲመለሱ ለመኗቸው። መላከ ብርሃን አድማሱ "ከአሁን በኋላ በቃኝ። ይህ ክፉ ዘመን ነው። ባምስቱ የመከራ ዘመን በጠላት የተገደሉትንና በራሳችን ወገኖችም በስቅላት የተገደለውን በላይን በሞት እስክቀላቀላቸው ድረስ የተረፈውን ዘመኔን እያለቀስኩ እፈጽማለሁ የመሪነቱን ስልጣን ተረከቡኝ" ብለው የደብሩን ሊቃውንትና አዛውንት ተማጸኑ። ሊቃውንቱና አዛውንቱ ደጋግመው በመመላለስ "ከእርሰዎ ጋር አልቅሰን እንሞታለን እንጅ አንለቅወትም" ብለው በመላቀስ ከጮለሚት ገዳም ወደደብሩ እንዲመለሱ አደረጉ።ከገዳም ወጥተው በተሰበረው መንፈሳቸው ደብሩን መምራታቸውን ቀጠሉ።

በተሰበረ መንፈስ የብቸና ጊዮርጊስን ደብር በመምራት ላይ ሳሉ ቀደም ብለው የሚያውቋቸው አዲስ አበባ ይኖሩ የነበሩት ሊቃውንታና አዛውንት "መላክ ብርሃን አድማሱ በብቸና አውራጃ ብቻ ከሚወሰኑ አዲስ አበባ መጥተው ቤተክርስትያኗን በሰፊው እንዲያገለግሉ ለመኗቸው።

መላከ ብርሃን አድማሱ አልተቀበሉትም። የመላከ ብርሃንን እውቀትና፣ የመንፈስ ልዕልናን ጥናት የተረዱት ሊቃውንትና አዛውንት ውትወታውን አላቆሙም። ንጉሡን ወትውተው በአምስቱ ዘመን ለፈፀሙት ያርበኝነት ተግድሎ ባለአምስት ኮከብ ያርበኝነት መዳሊያ በንጉሡ እንዲሸለሙ ተደረገ። መላከ ብርሃን አድማሱ ሽልማቱን በወቅቱ ተገኝተው እንዳልተቀበሉ ይነገራል።

***በበላይ ዘለቀ መሞት ጥልቅ ሐዘን ላይ መሆናቸውን የተረዱት ሊቃውንትና አዛውንት ሁላችንንም ባሳዘነ ሁኔታ በላይ ወ ደማይመለስበት ተሸኘቷል። እርሰዎ በማይመለስ ሰው ሐዘን አዕምሮዎን ቆልፈው ቀሪ ህይወትዎን በከንቱ አያባክኑ፤ በላይን በሰቀሉት ከሀዲዎች ምክንያት አምላክ ያደለዎን እውቀትና ችሎታ አገረዎንና ቤተ ክርስቲያነዎን አይንፈጉ። በመንፈስ ቢጎዱም አቅመዎ እስኪደክምና ይህችን ዓለም እንደነ በላይ በሞት እስኪለቋት ድረስ እግዚአብሄር የሰጠዎን ምክርና ተግሳጽ ለሀገረዎና ለቤተ ክርስቲያንዎ ከማበርከት ወደ ኋላ አይበሉ፤ እያሉ፤ ጣሊያን የሰበራቸውን አገራቸውንና ቤተ ክርስቲያቸውን እንዲጠግኑ ደጋግመው ተማጸኗቸው።***

***ከብዙ ውትወታ በኋላ የሊቃውንቱንና የአዛውንቱን ተማጽኖ ሰሙ። በዚህ የተደሰቱት ሊቃውንትና አዛውንትም ተጽዕኖ አሳድረው ከብቸና ደብር አዲስ አበባ እየተመላለሱ በቤተ በቤተ ክህነትና በጠቅላላ አገር ጉዳይም እንዲሳተፉ አደረጉ። እሳቸውን የሚተካ ለብቸና ቅዱስ ጊርጊስ መላከ ብርሃን እስኪሰየም ድረስ፤ ሊቀጠበብት ገዳሙ ተሻለ በሊቀጠበብት ነት መላከ ብርሃንን አድማሱን ወክለው ደብሩን እንዲያስተዳድሩ ተደረገ። መላከ ብርሃን የሊቃውንቱ ጉባዔ የመጀመሪያው ፕሬዝደንት ሆነው ጉባኤውን በመምራት በጣሊያን የተበላሸውን ማስተካከል ጀመሩ። መስተካከል ከሚገባቸውና ቅድሚያ ከሰጡት አንዱ የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስትያን ከኮፕቲክ ቤተክርስትያን ጋር የነበራት ግንኙነት ነበር። ጣሊያን ከመግባቱ በፊት የኢትዮጵያ ቤተክርስትያንን በበላይ እንዲመሩ ከግብፅ የተላኩት እኒህ ግብጻዊው አቡን ቄርሎስ ነበሩ።***



Abba Kyrillos
2nd of Primate of Ethiopia from June 1927 - 10th of October 19

***በጣልያን ወረራ ጊዜ እነ መላከ በርሃን አድማሱ ከአርበኞች ጋር ሆነው ሲዋጉ እነ አቡነ ጴጥሮስ ፋሽሽትን ተጋፍጠው ሲረሸኑ አቡነ ቄርሎስ ወደ አገራቸው ወደ ግብፅ ሸሹ። አቡነ***


ቄርሎስም ሆኑ የኮፕቲክ ቤተክርስትያን የኢትዮጵያ ሕዝብ በመርዝ ጪስ እያለቀ ድምጣቸውን ማጥፋታቸውና፤ በደስታና በሰላም ጊዜ አብሮ ኖረው ፤ በመከራ ጊዜ ጥለው መሸሻቸው በግብጽና በኢትዮጵያ መካከል በነበረው ህብረት ላይ ጥያቄ ፈጠረ።

ቅሬታ እጅግ ከተሰማቸው አንዱ መላከ ብርሃን ነበሩ። ቅሬታ ከተሰማቸው ኢትዮጵያውያንና ከንገሡ ጋራ በመተባበር፤ ከእንግዲህ ወዲያ በቤተክርስትያኗ የሚሰየሙት አቡኖች ህዝባቸውንና አገራቸውን ከውጭ ወራሪ ለመታደግ እንደ አቡነ ጴጥሮስ በደማቸው ማስመስከር የሚችሉ፤ በዜጎች ላይ በደል የሚፈጽም አመጸኛ መንግስት ሲከሰትም፤ እንደ ግብጾች አስተርጓሚ ሳይፈልጉ የህዝቡን የመጎዳት ስሜት ፈጥነው ተረድተው ወደ ገዳም በመመነን በሩቅና በቅርብ ላለው ሁሉ መልእክት የሚያስተላልፉ ኢትዮጵያውያን ዜጎች ብቻ እንዲሆኑ ከፍተኛ ትግል አደረጉ። ከብዙ ክርክር በኋላ ነገሩ ተሳካና በወረራው ዘመን በስደት ላይ የነበሩትን እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስን የመጀመሪያ ፓትርያርክ ሆነው ተ ሰየሙ።

ጵጵስናውን ከግብጽ በማላቀቀ አልተወሰኑም። ጣልያን በጦርና በመርዝ የኢትዮጵያን ሕዝብ በሚፈጅበት ጊዜ፤ በመንፈስና በሀሳብም እርስ በርሱ ለመከፋፈልና ለማዳከም አስከትሎ ባመጣቸው ሰባኪዎች በህዝቡ ላይ የደፋውን የነገረ መለኮት አተላ ለመጥረግ እቅዶች ተዘጋጁ። ከተዘጋጁት እቅዶች አንዱ የመማክርት ጉባኤን መመስረት ነበር።

መላከ ብርሃን በተመሰረተው መማክርት ጉባኤ በቀጥታ እየተሳተፉ የድርሰትና የታሪክ ክፍል ሀላፊነቱን ተረከቡ። ምዕራባውያን ካቶሊኮችና ፕሮቴስታንቶችን ቤተክርስትያኗን ለመከፋፈል የሸረበቱን ሴራ ለመበጣጠስና ለመመከት መጻሐፍት ጻፉ። በሮማ ካቶሊክ በኩል በቤተ

**ክርስቲያናችን ላይ የተከሰከሰውን ለማጽዳት መድሎተ አሚንን፤**







**በ በፕሮቴስታንት በኩል የገባውን ለመጥረግ ወጣት ተመልከት እንዳትሳሳት በሚል ማሰሰቢያ ኮኩን ሃይማኖት የሚባለውን መጽሐፍ አሳትመው፤ እነሆ ዛሬም በአጸደ ሥጋ በሌሉበት በኛ ዘመንም ለቤተክርስቲያናችን በመታገል ላይ ናቸው።**

**እግዚአብሔር የመላከ ብርሃን አድማሱን የብርታት መንፈስ በሁላችን ያሳድርብን!**

**መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ለጠቅላላዋ ኢትዮጵያ ያበረከቱትን ከዚህ ቀጥየ በማቀርባት ጦማር እንገናኝ።**

**መላከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ በዲቁን ማገልገል ከጀምሩበት ከዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ ሊቃውንት ጀመረው ከመላ ሊቃውንት አበው በሰበሰቡትን እውቀትና የሞራል ብቃት እየተደገፉ ከ1927 ሊቀ ጠበብት ሆነው ቀጥሎም በ 1936 አመተ ምህረት መላከ ብርሃን ተብለው ከተሰየሙ በኋላ ከጣሊያን ጋራ የተፋለሙበት፤ የጀግኖች የ ነበላይና የሊቃውንቱ አገር፤ እኔም ከፊደል ጀምሮ እስከ ቅኔው ድረስ እየተማርኩ ያደኩበት ታላቁ ደብር ብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ ይህ ነው።**